# ስለ ኢሮብ ህዝብ ታሪክ ያልተመለሱ ጥያቄዎች

ኃይለስላሴ ዮሓንስ

(ሞዱይሳ)

ኢሮብ በሰሜን ምስረቅ ኢትዮጵያ በትግራይ ክልል ምስራቃዊ ዞባ የሚገኝና ከኤርትራ ጋር የሚካለል አናሳ ብሄረሰብ የሚጠራበት ስም ነዉ፡፡ ይህ ስም በዉስጡ ቡክናይቲዓረ፡ሓሳባላዓረንና አድጋዲዓረ የተባሉና ከአንድ የዘር ግንድ የወጡ ህዝቦችን ያጠቃልላል።ህዝቡም በጥቅሉ አዱሓ ኢሮብ /ሶስቱ ኢሮቦች/ ተብሎ ሲጠራ ኖሯል። የኢሮብ አፈታሪክ አዋቂዎች ከአበው የተረከቡት የህዝቡ ታሪክ በአፈታሪክ ለትውልድ ሲያስተላለፉ ቆይቷል።

አንዳንዶቹ የኢሮብ አፈታሪክ አዋቂዎች፤ ለምሳሌ አቶ ሚካኤል ገብራይ ማይዳ ጸበቦ፣ ስለ አዱሓ ኢሮብ /ሶስቱ ኢሮቦች/ አሰያየም ሰፋ ያለ ትንተና ይሰጡ ነበር። በሳቸው አባባል በቀደምት ጊዜ፤ በዋናነት፣ አዱሓ ኢሮብ /ሶስቱ ኢሮቦች/ ተብሎ ይጠሩ የነበሩት በአሁኗ የኢሮብ ምድር የሚገኙና ሱመ የወለዳቸው፤ በከፊል ሰራየና አከለጉዛይ የሚገኙ ሰንበታይ የወለዳቸው፤ ኢንዲሁም በጽራዕና ወምበርታ የሚገኙ ሓንናከ የወለዳቸው ሶስትየዎሽ ናቸው እንጂ በአሁኗ የኢሮብ ምድር የሚገኙ የሱመ ልጆች ብቻ አለነበሩም። እነዚህ ሶስቱ ወንድማማቾች የወለዱአቸው የወረደምሕረት የልጅ ልጆች ደግሞ በየወቅቱ በሚጠራው የነገዳቸው ሸንጎ፤ በአሁኑ አጠራር ማይ - ጻዕዳ ተብሎ በሚጠራው ቦታ ይሰበሰቡ እንደነበር ይተርኩ ነበር። የዚህ እውነታ፣ የኢሮብ ታሪክ በባለሙያ የታሪክ ተመራማሪዎች፤ በሳይንሳዊ ዘዴ ይጠና ዘንድ መንግሰትና የኢሮብ ህዝብ በአንድነት የታሪክ ጠበብቶች በማሰማራት የኢሮብ ህዝብ ታሪክ ኢንዲጠና ሲያደርጉ የሚታወቅ ሆኖ ለአሁኑ ግን፣ በዚህ ጽሑፍ፣ ሲነገሩ የቆዩትን የተለያዩ አባባሎች ሳይሸራረፉ ለማቅረብ እሞክራሎህ።

በጅኦግራፊያዊ አቀማመጥ ሲገለጽ፤ የኢሮብ ህዝብ በሰሜን ምስራቅ በኩል ከሳሆ ብሄረሰብ፤ በሰሜን ምዕራብና በምዕራብ ከትግራይ ብሄረሰብ እንዲሁም በደቡብና በምስራቅ በኩል ደግሞ ከአፋር ብሄረሰብ ይዋሰናል።

ከዚህ በላይ እንደጠቀምኩት፣ ስለኢሮብ ህዝብ ታሪክ የተደረገ ሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር ባለመኖሩ ይህን ቀጥሎ የማቀርበው ጽሁፍ ምንጭ በአካል ያነጋገርኳቸው የኢሮብ ታላለቅ የአፈታርክ አዋቂዎችና ሁለቱ ስለ ኢሮብ ታሪክ በትግርኛ ተጽፈው የሚገኙ መጻህፍት ናቸው። አንቱታን ካተረፉት የኢሮብ ታሪክ አወቂዎች ውስጥ አንዳንዶቹ፤

ሀ. ከቡክናይቲዓረ፤ አቶ ዓዱዑማር ጎዕስን፤ አቶ ሚካኤል ገብራይ ሓውኩ፤ አቶ ሀይሉ ወልዱ ሞሲ ኮማን፤ አቶ ሐጎስ ማሳ ሓነይታን፤ አቶ ዳባሳይ ካህሳይ/ጎይላ/ና ሌሎቹም ሲሆኑ

ለ. ከሓሳባላዓረ፤ ባይሳይ ስበሓት እና ልጃቸው አቶ ሱባጋድስ ከሰረክለ /ዳታ አራዕ/

ሐ. ከአድጋዲዓረ ደግሞ ያባ ጊደይ ሓጎስ (ጊደይ ኡንዱዐ) የተባሉ የታሪክ አዋቂወችን ናቸው።

## ሳይሳካ የቀረ የመጀመርያው የኢሮብ ታሪክ ጥናታዊ ኮንፈረንስ

እነዚህ ከዚህ በላይ ስማቸው የተዘረዘሩት የአፈታሪክ አዋቂዎች በ1974/1976 ስለኢሮብ ታሪክ የሚነጋገር አንድ የኢሮብ ተወላጆች ኮንፈረንስ በዓሊተና ለማካሄድ በተደረገው ዕቅድ፤በወቅቱ

በሕይወት የነበሩት፣ በኮንፈረንሱ እንዲሳተፉና የበኩላቸውን እንዲያበረክቱ የመጀመርየ ቦታ ከተቸራቸው አንዳንዶቹ ነበሩ።

በዚያን ጊዜ፣ ለኮንፈረንሱ መሳካት የብዙ ሰው በጎ ፍላጎት የተንጸባረቀ ከመሆኑ ባሻገር እያንዳንዱ በንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ የዓሊተና ነዋሪ በነፍስወከፍ ብር 50 ለማዋጣትም ተዘጋጅቶ ነበር።ይህን የተቀደሰ ሃሳብ ተግባራዊ እንዲሆን በግንባር ቀደመትነት የተሰለፈው የዓሊተና ልደታ ለማርያም መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመምህራን ቡድን ሲሆኑ ከዓሊተና ገዳም ደግሞ አባ አለማ ጊደይና አባ ፋሱሕ በረሀ የሃሳቡ ቋሚ ምሰሶ ነበሩ። አባ ሓጎስ ገብሩም ምክርና ሃሳብ በመስጠት ተሳታፊ ነበሩ።ሲስተር ዘወይ የተባሉና በወቅቱ በዓሊተና የዶተርስ ኦፍ ቻሪቲ የተባለ በጎ አድራጊ ድርጅት ሥራ አስከያጅ የነበሩ ደግና አስተዋይ ሓላፊ ደግሞ ለኮንፈረንሱ መሳካት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ለማበርከት ዝግጁ መሆናቸው አረጋግጠው ነበር። ሆኖም ግን በወቅቱ አከባቢያው፤ ግፈኛውን የደርግ ሥርዓት ለመጣል ይካሄድ የነበረውን የትግራይ ህዝብ ትግል ይመራ በነበረው የትግራይ ህዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት ቁጥጥር ሥር በመኖሩና ከደረግ ወታደረዊ የጦር ኃይል ጋር በመፋለም ላይ ስለነበረ፤በሁለቱ መሃከል ይካሄድ በነበረው ጦረነትና አለመረጋጋት ምክንያት ለውጤት ሳይበቃ ቀረ።

ጉዳዩ እንዲህ ነው። በተለይ በቡክናየቲዓረ "ህዝቢ - ክፍሊ" ሆኖ የአስተዳደር ጉዳዮችን እንዲከታተል ተመድቦ ይሠራ የነበረው አስፍሓ የተባለ ደግና አስተዋይ እንዲሁም ትዕግሰተኛ የትግራይ ህዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት ታጋይና ተወካይ ኮንፈረንሱን ለማካሄድ ጥያቄ ሲቀረብለት ጉዳዩን ለበላይ አሳውቆ ከተነጋገረበት በኋላ መልስ እንደሚሰጠን ነገረን። መልስ ማግኘቱ ወራትን ያስቆጠረ ቢሆንም የተገኘው ምላሽም ቢሆን ፈታኝ ነበር።መልሱም፣ ኮንፈረንሱን የትግራይ ህዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት ታዛቢዎች ወይም ተወካዮች በተገኙበት ማካሄድ እንደሚንችል ሲያበስር የኮንፍረንሱ ውጤት ወይም ማጠቃለያ ሃሳብ ደግሞ በትግርኛ ተጨምቆ ኢንዲዘገብ የሚል ነበር።ለኮንፍረንሱ አዘጋጆቹም ሆነ ሃሳቡን ለሚደግፉ ወገኖች ግን የተሰጠው መልስ ፈታኝ ነበረ። ምክንያቱም በዚሁ ኮንፈረንስ ጦስ በትምህርት ቤቱ አስተዳደርና አባላት እንዲሁም በብዙ ድካምና አስተዋይ ልቦና የተገነባውና ለመላው የኢሮብ ህዝብ የብርሃን ጮራ የሆነው፤ኢንዲሁም በብዙ መስዋእትነት የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴውን በሚተገብረው ታሪካዊው የልደታ ለማርያም ትምህርት ቤት ላይ፤ አፋኙ የደርግ ሥርዓት የትግራይ ህዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት ታዛቢዎች ወይም ተወከዮች በኮንፍረንሱ መሳተፍ ምክንያት አድርጎ ሊያደርስ ለሚችለው ጥቃት ላለማጋለጥ ኮንፈረንሱን ላለማካሄድ ተወሰነ። በዚህም ምክንያት ከፍተኛውንና የመጀመርያውን የኢሮብ ህዝብ ታሪክ ኮንፈረንስ የማዘጋጀት ጥረት የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ። ምክ ንያቱም የህዝብ ክፍል የነበረው ታጋይ አስፍሃም፤ የድርጅቱ ውሳኔም ቢሆን የማይቀለበስ መሆኑ ን ደግሞ ስላስረገጠ ነበር።

## ያልታቀደ የኢሮብ ታሪክ ሰሚናር

የመጀመረያው የኢሮብ ታሪክ ሰሚናር ተግባራዊ የሆነው በኢትዮጵያ ርእሰ ከተማ በአድስ አበባ በ1984/85 ዓ.ም በካቶሊካዊት ቤተክርሰትያን ካቴድራል የምእመናን አደራሽ ነበር።በሴሚናሩም ሶስት ጽሁፎች ቀርበው ነበር።

ለሰሚናሩ መነሻ ሃሳብ የሆነው ዋናው ምክኒያት በወርሓ ግንቦት 1983 ዓ.ም የደርግ ሥርዓትን አሽቀንጥሮ የጣለው የኢትዮጵያ ኅዝባዊ ኣብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር/ኢኅአዴግ/ የክልል መስተዳድርን ሲያዋቅርና፤ በትግራይ ክልል የሚገኙ ብሄር ብሄረሰቦችን ሲተነትን ትግራዋይንና፤ኩናማን፤ በትክክል በስማቸው አስፍሮ ሲያበቃ፤ የኢሮብ ብሄረሰብን ግን የሳሆ ብሄረሰብ ብሎ በመሰየሙ ነበር።

በወቅቱ ከፍተኛ የሃሳብ መንሸራሸር የታየበት መለስተኛ ውዝግብ የኢሮብ ልጆችን ለሁለት ጎራ ከፍሎ ነበር። የሃሳብ ልዩነቱ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ በመውጣቱ ለመላው የጋዜጣው አንባቢ ኢትዮጵያዊም ተዳርሷል። አንዱ ወገን የኢሮብ ብሄረሰብ መጠሪያ ሳሆ መሆን አለበት ብሎ ሲጽፍ ሌላው ወገን ደግሞ የኢሮብ ብሄረሰብ መጠሪያ ኢሮብ መሆን አለበት በማለት የክርክር ጭብጡን ሲቀልም ነበር። በአዲስ አበባና ዙርያው ነዋሪ ከነበሩት ውስጥ፤ እኛ ኢሮብ ስለሆን መጠርያችን ኢሮብ መባል አለበት ብሎ ይከራከር የነበረው ክፍል፣ ድመጽ ወይም ስሜት በግንባር ቀደምትነት ይስተጋባ የነበረው በተከበሩ በአቶ ኃይለሥላሴ ገብራይ ነበር። ሌላኛው ወገን ግን በጋዜጣው ላይ በሰጠው የሃሳብ ክርክር የብዕር ስም በመጠቀሙ ምክንያት ራሱን ግልጽ ሳያደርግ ነበር እምነቱን ያንጸባርቀው።

በዚያን ሂደት፣ የዝህ የብሄረሰቡ የስም ስያሜ ጉዳይ፣ ጊዜና አጋጣሚ ያገኘ የኢሮብ ተወላጅን በሙሉ በያለበት ቦታ ያነጋገረ ነበር።ውይይቱም፣ በመቀሌ፣ በዓዲግራትና፣ በኢሮብ ምድር ሁሉ በስፋት ተካሄደ።

በዝህ ውዝግብ መነሻ ምክንያትም፣ በአዲስ አበባ ይኖሩ የነበሩ አብዛኞቹ የኢሮብ ተወላጆች በተገኙበት በተከሄደ ሰሚናር ሶስት ጽሁፎች ቀርበው ነበር።የጽሁፎቹ አቀራቢዎችም፤

1. አቶ ኃይለስላሴ ገበራይ / የብላታ ገብራይ ወልደሥላሴ ልጅ/
2. ዶክተር ተስፋይ ኃይለማርያም /ቀያፉ/
3. አቶ ተስፋማርያም በረሀ /ሓሊቦ/

ከዚህ በመቀጠልም፤ ይህ ጽሁፍ የእነዚህ ሱስቱ ጽሁፎች ሃተታ፤ ዋናዎቹ የአገርቤቶቹ የኢሮብ የአፈታሪክ አዋቂዎች ከሚሉት ጋር በማገናዘብ ያቀርባል።በጥቅሉ አንኳር አንኳር ሃሳቦቹን ለመጥቀስ ያህል፤

አቶ ኃይለሥለሥላሴ ገብራይ፤ የኢሮብ ታሪክን፤ አብዛኖቹ ቀደምት የኢሮብ አበው እንደሚተነትኑት ሁሉ፤ በክብረ - ነገሥት ላይ ሰፍሮ ከሚገኘው ታሪክ፣ ማለት የኢትዮጵያ ንግስት የነበረችው ንግስተ ሳባ ንጉሥ ሰለሞንን ከመጎብኘት አፈ ታሪክ ጋር በማያያዝ መተንተኑን ተያያዙት።ከዝያም ንግሥት ሳባ ከንጉሥ ሰለሞን ጸንሳ ስትመለስ፣ ማይበላ በተባለው ወንዝ ዳረቻ የወለደችውን ቀዳማዊ ሚኒሊክ አባቱን ለመጎብኘት ሄዶ ብዙ የሚነገርለትን ታቦተ ጸዮን (The ark of covenant) ይዞ ሲመለስ፤ ከሱ ጋር አብሮት ከመጡት መሃል ውስጥ፣ የንጉሥ መግድር እና የንጉሥ ሰለሞን እኅት የሆነችው የንግሥት ኢሌኒ ልጅ የሆነው የልዑል እስክንድር ዘር ናቸው ኢሮቦች በማለት ነበር መሠረቱን ያስቀመጡት። በመቀጠልም የልዑል እስክንድር ማረፊያ ጽራዕ ወምበርታ ተብሎ በሚጠራው የትግራይ ክልል በምሥራቃዊ ዞባ፣ በክልተ አውላዕሎ፣ በአጉላዕና አከባቢው ባለው ሰፊ መሬት እንደነበረ በመጥቀስ የእኚህ የልዑል እስክንድር የዘር ዘር የሆነው ወረደምሕረት፤ ሰንበታይ ሓንናከ እና ሱመ የተባሉትን ሶሰት ልጆቹን ይዞ አሁን የኢሮብ ልጆች ሰፍረውባት ወደምትገኘው መድር ስላደረገው ጉዞ አብራሩ። በመጨረሻም ሱመ የአሁኑ ሶስቱ ኢሮቦች ያፈራ ሲሆን፤ ሓንናከ ወደ ትውልድ ቀዮው ተመልሶ አሁን በጽራዕ ወምበርታ በአጉላዕና አከባቢ ለሚኖረውን ህዝብ አባት ለመሆን መብቃቱን በመግለጽ ሰንበታይ ደግሞ በዛሬይቷ ኤርትራ በአክለጉዛይና በሰራየ የሚገኙትን ህዝበች በከፊልም ቢሆን ያፈራ መሆኑን የሚያስረዳ ትንተና አቀረቡ። ይህም አባባል በይዘቱ፤ አባ ትስፋስላሴ መድህን (1993)፤ *ታሪኽ ኢሮብ / ሓጺር መግለጺ፣* በአማርኛ ሲተረጎም ደግሞ፤ የኢሮብ ታሪክ/አጭር መግለጫ /፤ (ትርጉም የኔ ነው) ከሚለው እና መምህር በርሀ ዝግታ (2000)፤ *መበቖልን ታሪኽን ህዝቢ ኢሮብ፣* በአማሪኛ ሲቶረጎም ደግሞ፤ የኢሮብ ህዝብ ታሪክና መሰረት፤ (ትርጉም የኔ ነው)፣ ከሚለው ጋር የማይራራቅ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ዶክተር ተስፋይ ኃይለማርያም /ቀያፋ/ ኢትዮጵያን ቀደም ብለው የዳሰሱና ስለ አደረጉት ጉዞና ስለ አካበቱት እውቀት በጽሁፍ የዘገቡትን የጣሊያንና የሌሎችም አገሮች ጸሓፍትና መጻሕፍት በማጣቀስ የኢሮብ ታሪክ መሰረቱ የደንከል ህዝብ መሆኑን ሲያትቱ አደራሹ ውስጥ የነበረው የኢሮብ ተወላጅ በመገረም ነበር የተከታተለው። ስለ ዶክተሩ አንድ እውነታ መታወስ ያለበት ቢኖር፣ በኢትዮጵያ ቢሄረሰብ ኢንስቲቲዩት ይሠሩ በነበረበት ወቅት፣ በኢሮብ ታሪክ ምርምር ላይ ጊዜ ሰጥተው ሲደክሙበት የኖሩ ምሁር መሆናቸውን ነው። በአንድ ወቅት ብዛት ያላቸው ልዩ ልዩ የኢሮብ ዓዳር /ግጥሞች/ አሰባስበውና በጽሁፍ አስፍሮ ለህትመት ለማብቃት በዝግጅት ላይ እንዳሉ አስተያየቴን እንዳሰፍርበት ጠይቀውኝ በእኔ በኩል እጹብ ድንቅ መሆኑን በመግለጽ ከልቤ አድንቄላቸው ነበር።ጽሑፉ ለኅትመት ስለመብቃቱና አለመብቃቱ ግን ለማወቅ አልቻልኩም።

በዶክተሩ የኢሮብ ታሪክ አዘጋገብ ዋናው ፍሬ ሃሳብን በተመለከተ ግን፤ ማለት በወቅቱ ስለኢሮብ ታሪክ አመጣጥ የሰጡት ትንተና፣ ለብዙወቻችን የኢሮብ ተወላጆች አዲስ ነበር። የዶክተር ተስፋይ(ቀያፋ) የምርምር ውጤት የሆነውና የኢሮቦች ከደንከል ህዝብ መፍለቅ የሚገልጽ ታሪክ መቀበሉ ዳገት ነበር የሆነብን። የለም፣ እንዲህ ነው ብለን ለመከራከር ግን በጥናት ላይ የተሞረከዘ የታሪክ ጭብጥ ማቅረብ ስላልቻልን ደግሞ ዝምታውን ለመምረጥ ተገደን ጭጭ አልን።

ሶስተኛው ወረቀት ያቀረቡት አቶ ተስፈማርያም በርሀ (ሃሊቦ) ስለ ኢሮብ ህዝብ ታሪክ መሠረት ሲገልጹ የሃሳብ ክርክሩን የቆረቆሩት፤ የአሁኑ ኢሮብ ብሄረሰብ ተወላጆች በአንድ ወቀት ትግራያዊያን ነበሩ በሚል ንድፈ ሃሳብ ላይ ነበር። በአቶ ተስፋማርያም አባባል ወረደምሕረትና ልጆቹ ምክንያቱ ባልታወቀ ጉዳይ ከቀድሞ መኖርያቸው ከጽራዕ ወምበርታ ወደ ዛሬይቱ የኢሮብ ምድር እንደመጡ አቶ ኃይለሥላሴ ገብራይ ከአቀረቡት ከአብላጫው የኢሮብ ህዝብ እምነት ጋር አንድ ሲሆን፤ በእሳቸው አባባል፤

> ወረደምሕረትና ልጆቹ ወደ ዛሬይቱ የኢሮብ ምድር ሲሰደዱ ቀድመውም ትግሪኛ ተነጋሪዎች ነበሩ። በቦታው ላይ ሲደርሱ ላገኙአቸው በአከባቢው ይኖሩ ለነበሩት ሳሆ ተናጋሪዎች፤ ይህ አገር ምን ይባላል? ብለው ሲጠይቁዋቸውም፤ ነዋሪዎቹ፣ እንደልማዳቸው፣ ለእንግዳ ሁሉ መልካም አቀባበል ሲሉ ሲገልጹ እንደቆዩት ሁሉ፤ ”ኦሮባ” /እንኳን በደህና መጣቹህ/ በማለት መልስ ሰጡአቸው።ወረደምሕረትና ልጆቹም ለጠየቁት ጥያቄ መልስ ያገኙ መስሎአቸዉ፤ ማለት የሳሆ ቋንቋ ካለመረዳት፤ አከባቢውን ኢሮብ ራሳቸውንም የኢሮብ ምድር ነዋሪዎች ኢንደሆኑ ተቀበሉ። በዚያውም ቀስ በቀስ ሳሆ ተናገሪ ትግራያዊያን ሆኑ። ስለሆነም የዛሬ ኢሮቦች የትናንትና ትግራያዊያን ናቸው፤

በማለት ለታዳሚው ጭረሽ አዲስ የኢሮብ ህዝብ ታሪክ አስደመጡ። ተሰብሳቢውም በመገረም የሚለውን አጣ።

የአቶ ተስፋማርያም የኢሮብ ታሪክ ትንታኔ ቀድሞአቸው ከቀረቡት ሁለቱ ጥናቶች የሚለይበት ዓይነተኛ ነገር ቢኖር ግን ለማመሳከርያ የሚጠቅሱት ክብረ - ነገሥት፤ መጸሓፍ፤ ወይም ሰው አለመኖሩን ነው። ይሁን እንጂ እንደ መላምት ግን፤ አቶ ተስፋማርያም ያቀረቡትን ትንታኔም ቢሆን፣ ውድቅ ለማድርግ ቀላል አለመሆኑንና፤ ስለሆነም የኢሮብ ታሪክ በቅጡ በባለሙያዎች መጠናት እንዳለበት ታዳሚው ሁሉ በዓይነ - ኅሊናው ተስማማ።

ይሁን እንጂ አንጋፋዎቹ የኢሮብ አፈታሪክ አዋቂዎች፤ ለምሳሌ አቶ ሚካኤል ገብራይ ማይዳጸበቦ እና አቶ ጊደይ ሃጎስ (ኡንዱዐ)፤ የአቶ ተስፋማርያምን አባባል ከሥረ - መሠረቱ የሚጻረር የኢሮብ ታሪክ ትንታኔ ይሰጡ ነበር። መላው ዓጋመ፣ ጉለማካዳ፣ ሳባያ፣ መኖኽሶይቶ፣

ሽመዛና፣ ናድወ ወዘተ በእነሱ ዕድሜ፤ በከፊልም ቢሆን ወይም አልፎ አልፎ በየቦታው ኢሮብ /ሳሆ/ ተናገሪ ይገኝ እንደነበረ ምስክርነታቸውን ሰጥተውኛል።በእነዚህ የኢሮብ አፈ ታሪክ አዋቂዎች አባባል በአሁኑ ጊዜ ያ ሁሉ አልፎ ተርፎ የኢሮብ አንኳር የነበሩት እነ ማድዓና ካረዳ እንዲሁም ማይጺዓ፤ ኢሮብነታቸው በትግራዋይ ቋንቋና ባህል ተደፍጥጦ ይገኛል ሲሉ የሃሳብ ክርክራቸውንም ያቀርቡ ነበር። ስለሆነም የታሪክ ምስክረነት የሚያሳየው የኢሮብ - ሳሆ ተናጋሪ ህዝብ ይሸፍነው የነበረው የቆዳ ስፋት ከጊዜ ወደ ገዜ እሳት እንደነካው ላስቲክ እየተኮማተረ ወደ እጅ መዳፍ ወደምታክል ወረዳ መጨፈልቁን ነው። በዚህ ዙርያ፣ በቀጣይነት ሰፊ የአከባቢው ዕውቀት ያላቸው ተመራማሪዎችና ጸሓፍት አንዳንድ ጠቀሚ ዕውቀት እንደሚያካፍሉን እምነቴ ነው።

እለይ እንደተገለጸው የአዲስ አበባው ሰሚናር የተካሄደው በእቅድ ሳይሆን በወቅቱ ለኢሮብ ህዝብ የተሰጠና ህዝቡ የማያምንበትና የማይስማማበት አዲስ የስም ስያሜ ምክንያት ነበር፤ የሳሆ ብሄረሰብ ብሎ መሰየም። በዝህም ምክንያት፤ከላይ በዝርዝር እንዳመላከትኩት የኢሮብ ተወላጆች ጩኸት በያለበት በረከተና በረታ። መንግስትም እግዝአብሄር ይስጠውና የህዝቡን ጩኸት ሰማ። የብሄረሰቡ መጠሪያም ከጥንት ከጥዋቱ እንደቆየው እንደበፊቱ ኢሮብ ብሄረሰብ ተብሎ እንዲጠራ ሲል መንግሥት ማህተሙን አስፈረበት። የኢሮብ ህዝብም ስሙ ስለተከበረለት ደስ አለው።

## ታዲያ ያልተመለሱ ጥያቄች ምንና ምን ናቸው?

ስለ ኢሮብ ህዝብ ታሪክ ያልተመለሱ ጥያቄዎች እጅግ ብዙ ናቸው። ምክንያቱም የተመለሰ ጥያቄ የለምና።ስለሆነም፣ ከዚህ በላይ ከቀረቡት ሶስት ጽሑፎች ውስጥ እንኳ የቱ ነው እውነቱ?ብልን ብንጠይቅ፤ መልሱን ለማግኘት ቀላል አለመሆኑ ግልጽ ነው። ለምሳሌ፤ አንደኛ፣ ኢሮቦች ሳሆ ተናጋሪ ትግራያዊያን ናቸውን? እንዴት? ሁለተኛ፤ኢሮቦች እውነት ከደንከል የፈለሱ ናቸውን? አይደሉም ካልን አለመሆናቸውን እንዴት እናመሳክራለን? አዎ ናቸው ብንልሳ? በመጨረሻም፣ ኢሮቦች የወረደምሕረት ልጆች፣ ብሎም የሱመ ልጆች ናቸው፤ የሚለውን መላምት እንኳ ብንቀበል፣ እንዲሁም በዛሬይቷ የኢሮብ ምድር ሱመ ከመምጣቱ በፊት፣ ቢያንስ ***ካያይታ*** የተባለ የራሱ ንጉሥ የነበረው ኃይለኛ ነገድ ነበረ ካልን (አባ ትስፋስላሴ መድህን 1993 እና መምህር በርሀ ዝግታ፣ 2000) እንዴት በዚች የአሁኗ የኢሮብ ምድር የሚገኘው ትውልድ ኢሮብ ብቻ ሊሆን ይችላል? ምክንያቱም የሱመ ልጆች ተባዝተው በዙ እንኳ ቢባል ቢያንስ ከነባሩ የአከባቢው ህዝብ ጋር በመዋሃድና በመዋለድ መሆን የለባቸውንምን ወይስ ለብቻቸው?

ከዚህም በተጨማሪ በኢሮብ ምድር ከካያይታ በፊት ይኖሩ የነበሩ ነገዶች ወይም ህዝቦች፡ ለምሳሌ እንደነ ***ደባዓ፣ ሑጉጉሞ*** ወዘተ የተባሉ ነገዶች ስለመኖራቸው የሚዘግቡ አፈታሪኮች ስላሉ፤ የእነዚህ ህዝቦች ታሪክ በኢሮብ ህዝብ ታሪክ ላይ ያለው እንድምታ ምን ሊሆን ይችላል? በኢሮብ ምድር፣ በተለያዩ ቦታ የሚገኙ ***ካራንሓሲት*** / አጀብ ባሉ የድጋይ ክምርና አፈር ድብዳብ በአከባቢው ካለው መሬት ተለይቶና ከፍ ብሎ የሚገኝ፣ በውል መቃብር ይሁን ወይስ የቤት ቁሳቁስ ወዘተ የተቀበረበት መሆኑ የማየታወቅ፤ በቦተው ላይ ለብዙ ዓመታት የዘለቁ ነገሮች/ የሚሰጡት የታሪክ ምስክርነተስ ምን ሊሆን እንደሚችል እንዴት መገመት ይቻላል?

ለዚህ ሁሉ ዓይነተኛ መልስ ሊሆን የሚችለው ዋነኛው ፍሬ ሃሳብ፣ በአቶ ሚካኤል ገብራይና በአቶ ጊደይ ሃጎስ (ዑንዱዐ) የኢሮብ ታሪክ አዘጋገብ ላይ በመሞረከዝ፤ ከብዙ ዓመታት በፊትና በቅርቡ ዓመታትምኳ ቢሆን፣ ዓጋመ፣ የእነ ወልዱ እና የእነደጊያት ሱባጋድስ መናሃርያ በነበረበት ጊዜ በአከባቢው ይንጸባረቅ የነበረው ሂደት በዓይነ ሂሊናችን ወደ ኋላ መለስ ብለን ስንመለከት፡ የሴም ነግዶች ቋንቋና ባህል አከባቢውን ሲገዛ በቆየው የኢሮብ ወይም የሳሆ

ባህልና ቋንቋ ላይ የበላይነቱን ይዞ እየዋጠው መሄዱን ነው። ለዚህም እንደምስክርነት ሊሆን የሚችለው፣ ለምሳሌ፣ ዝነኛው ደግያት ሱባጋድስ፣ ከኢሮብ የሓሳባላዓረ ልጅና የኢሮብ ቋንቃ ወይም ሳሆ ተናጋሪ ሆነው፤ ትግሪኛ ተነጋሪ ኢሮብ/ሳሆን እና ትግሪኛ የማይናገረው ኢሮብ/ሳሆንም ጭምር ባንድነት ሲያስተዳድሩ መኖራቸውን ነው። ከዚህም በተጨማሪ በደጊያት ሱባጋድስ ግዛት፤ ብላታን ጌታ ሆነው ያስተዳድሩ የነበሩት ታዋቂው ብለታ ፉሱሕ ወለደጊዮረግስ የአድጋዲዓረ ተወላጅ፣ ኢሮብ መኖራቸውን ነው።

ስለሆነም፤ ለማጠቃለል ያህል፤ በእኔ እምነት፣ አቶ ሚካኤል ገብራይና አቶ ጊደይ ዑንዱዐ እንዳሉት ሁሉ፣ ኢሮብ/ሳሆ ተናጋሪ በዓጋመና አከባቢው ከጥንት የኖረ ህዝብ ሲሆን፤ በዝህ ህዝብ ላይ የተካሄደው ዘገምተኛ ለውጥ ቢኖር፤ የህዝቡ የድሮ ቋንቋና ባህል በኤኮኖሚ የበላይነቱን በያዘው በሴም ቋንቃና ባህል እየተዋጠ መሄዱንና ነባሩን የኢሮብ/የሳሆ/ ቋንቋ እየተዳከመና የነበረውን መሪ ቦታ እያጣ ማዝገምን ነው። ከጊዜ በኋላም፣ አሁን ወደምንገኝበትና የኢሮብ/ሳሆ/ ተናገሪ አናሳ ብሄረሰብ ወደ ሆነበት ደረጃ ተደረሰ። በዚሁ አካሄድ ከቀጠለ ደግሞ ጭራሽ የኢሮብ ብሄረስብ ወደሚጠፋበት ደረጃ ሊደረስ እንደሚችል የሚያመላክት እውነታ እንዳለ ይስተዋላል። ስለሆነም መንግሰትና የኢሮብ ህዝብ በአፋጣኝ ለዚህ አሳሳቢ የኢሮብ ብሄረሰብ የህልውና ጥያቄ አስቸኳይና አጣዳፊ እርምጃ ቢወስዱ በኢሮብ ህዝብ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ስፍራ እንደሚኖራቸው አያጠራጥርም።ለዚህ ለተቀደሰ አላማ ዋና መንደርደርያ ሊሆኑ ከሚችሉ ቀዳሚ ክንውኖች ውስጥ፤

1. በኢሮብ ምድር በሚገኙ ትምህርትቤቶች ሁሉ ኢሮብኛ /የሳሆ/ ቋንቋ እንደመደበኛ ትምህርት እንዲሰጥ ቢደረግና ለዚሁ የሚሆን የትምህርት መገልገያ ቀሳቁስ በአስቸኳይ እንዲዘጋጅ ቢደረግ፤
2. በኢሮብ ምድር በሚገኙ በአንደኛና በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህረት ቤት የሚሰጠው መደበኛ ትምህርት በኢሮብኛ /የሳሆ/ ቋንቋ እንዲሰጥ ቢደረግና ለዚሁ የሚሆን የትምህርት መገልገያ ቀሳቁስ በአስቸኳይ እንዲዘጋጅ ተደርጎ መርሃ ግብሩም በአፋጣኝ በተግባር እንድውል ቢደረግ፤
3. ማንኛውም በኢሮብ ብሄረሰብ ውስጥ የሚከናወን የአስተዳደር ተግባር ሁሉ በኢሮብኛ /በሳሆ/ ቋንቋ እንዲከናወን በጥብቅ ቢሠራበት፡፡
4. ከዚህ ቀደም እነ አባ አብርሃም ሀይሉ ያሉበት ኮሚቴ እንዳቀረበው ገንቢ ሃሳብ ሁሉ የኢሮብ ህዝብ የመሰረታዊ ትምህርትና የዜና ሽፋን የሚያገኝበት በቋንቋው የሚተላለፍ የሬድዮ ፕሮግራም ስርጭት ቢተገበር መልካም ጅምር እንደሚሆን የብዙሃኑ የኢሮብ ተወላጆች ስምምነት እንደሆነ እምነቴ ነው።

**ማገናዘቢያ** (References)


አባ ተስፉይ መድህን፤ 1993፤ ታሪኽ ኢሮብ/ ሓጼር መግለጺ/ ዓዲግራት

መምህር በርሀ ዝግታ፤ 2000፤ መበቖልን ታሪኽን ህዝቢ ኢሮብ



ኃይለስላሴ ዮሓንስ

(ሞደይሳ)